የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፴
አዲስ አበባ የካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 30
ADDIS ABABA - 5th March, 1997

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፻፮/፲፱፻፺ ዓ.ም
ለሁለተኛው የኢነርጂ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ........................ ገጽ ፯፻፳፪

## CONTENTS

Proclamation No.106/1998
International Development Association Credit Agreement for Financing the Second Energy Project Ratification Proclamation ........................ Page 722

### አዋጅ ቁጥር ፻፮/፲፱፻፺
### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለምአቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለሁለተኛው የኢነርጂ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ.ዲ.አር. ፻፵፮ ሚሊዮን ፻ ሺህ (አንድ መቶ አርባ ስድስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር.) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፰ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመ በመሆኑ ፣

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

### PROCLAMATION NO. 106/1998
### A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

WHEREAS, a Development Credit Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit amount of one hundred forty six million one hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 146,100,000) for financing the Second Energy Project, was signed in Washington D.C., on the 25th day of January, 1998;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Credit Agreement at its session held on the 5th day of March, 1998;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለሁለተኛው የኢነርጂ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፮/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ·ኤ·አ· ጃንዋሪ ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፰ በዋሽንግተን ዲ·ሲ· የተፈረመው ቁጥር ፫ ሺህ ፲፱ ኢ.ት የብድር ስምምነት ነው።

፫· <u>የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ኤስ·ዲ·አር ፩፻፵፮ ሚሊዮን ፩፻ ሺህ (አንድ መቶ አርባ ስድስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ ኤስ·ዲ·አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the 'International Development Association Credit Agreement for Financing the Second Energy Project Ratification Proclamation No. 106/1998.''

2. *Definition*

In this proclamation ''Credit Agreement'' means the Credit Agreement No. 3019 ET signed in Washington D.C. on the 25th day of January, 1998 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of one hundred forty six million one hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 146,100,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 5th day of March, 1998.

Done at Addis Ababa, this 5th day of March, 1998.

NEGASO GIDADA(DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ድርጅት

BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE